# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 52 ግንቦት 6 2001 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

**ወያኔ ስለሰላም እየዘመረ የሰላምን እርግብ ተኩሶ የገደለ አረመኔ ነዉ። በግንቦት ሰባት እምነት ከወያኔ ጋር ‹‹ሰላማዊና ሰላማዊ ትግል ብቻ!›› ብሎ ጫወታ ዉጤቱ የወያኔን የሥልጣን፤ የኢትዮጵያችንና የታጋዮቻችንን መከራ ማርዘም ነዉ.....**

**ወያኔ ድፍረት አግኝቶ ራሱን ተፎካካሪም፣ ድምፅ ቆጣሪም፣ ዳኛም መሆኑ ማስቀረት በሚቻልበት መንገድ ይደራደር እንላለን። ወያኔ እራሱን ማዳን የሚችልበት ሰላማዊ አማራጭ ይህ ብቻ ነው።**

ከዝግጅት ክፍላችን

## የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤትን የሚኮንነው የውያኔ ውንጀለ በሃስት ምስክሮችና በውሸት የተሞላ ነው

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ላይ ያወጣውን ሪፖርት በማጥቃት ወያኔ፣ ሰሞኑን በኢትዮጵያ ቴለቪዥን ላይ ያቀረበው ተከታታይ ምላሽ በሃሰት ምስክሮች እና በውሸት የተሞላ መሆንቱ ተዘገበ

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ላይ ያወጣውን ሪፖርት በማጥቃት ስራ ላይ ተጠምዶ ያለው ወያኔ፣ ሰሞኑን በኢትዮጵያ ቴለቪዥን ላይ ያቀረበው ተከታታይ ምላሽ በሃሰት ምስክሮች እና በውሸት የተሞላ መሆኑ ተጋለጠ።

የሚይዘው የሚጨብጠው ጠፍቶት ሳር ቅጠሉን ሁሉ በማጥቃት ስራ ላይ ተሰማርቶ ያለው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፣ ሰሞኑን በተከታታይ የአገዛዙ የሃሰት መረጃ አቀባይ በሆነው በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ላይ የአሜሪካን መንግስትና የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ሁኔታ ላይ ያወጣውን አመታዊ ሪፖርት ሲያጠቃ እና ሲሳደብ መሰንበቱ ይታወቃል። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በአገሮች የሰብዓዊ መብት አያያዝ ላይ አመታዊ ሪፖርት እንደሚያወጣ እና በዚህ አመት በኢትዮጵያ ላይ ያወጣውም እንዳለፉት አመታት፣ አያሌ የመብት ረገጣዎችን መዘርዘሩን ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል።

ለዚህ የካቲት 18 ለወጣው አመታዊ ሪፖርት ወያኔ በወቅቱ አንድ አሳፋሪ ምላሽ መስጠቱንም ዘግበን ነበር። ነገር ግን ያ ከሆነ ከሁለት ወራት በኋላ፣ ሰሞኑን በደረሰበት መርበድበድ ግራ የተጋባው ወያኔ ሌላ ምላሽ አሳፋሪ አዘጋጅቶ ብቅ ብሏል። ይህ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ላይ በተከታታይ የቀረበው ፕሮግራምም አሳፋሪ፣ በተራ ስድብ የተሞላ እና አስቂኝ በሆነ ሁኔታ የአገዛዙን የሰብዓዊ መብት አያያዝ ከአሜሪካ ጋር ለማወዳደር የሚሞክር ተብሎ በብዙዎች ሲተች ሰንብቷል።

በፕሮግራሙ ላይ ወያኔ የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት እንደ ዋሸ እና በተሳሳተ መረጃ ላይ ተንተርሶ ሪፖርቱን እንዳዘጋጀ አድርጎ ለማሳየት ምስክር ተብዬዎችን ሲያቀርብ እና ራሱ የሰራውን ምርመራ በማሳየት ሲኳትን እንደቆየ ይታወቃል። ከቀረቡት ምስክር ተብዬዎች አንዱ የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ ፓርቲ እና የፓርላማ አባል አቶ ጌቱ ሙሊሳ ወንድም ነኝ የሚል ሲሆን፤ የስራ ድርሻውም ስለ አቶ ጌቱ በአገዛዙ ካድሬዎች መደብደብ የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሪፖርት የፃፈው ሃሰት ነው ብሎ ማስረዳት ነበር።

ባለፈው ሳምንት አቶ ጌቱ ሙሊሳ በሁለት ሌላ የፓርላማ አባላት ምስክርነት ታግዘው፥ ወንድማቸው ነኝ ብሎ ቴለቪዥን ላይ የቀረበውን ሰው ፈጽሞ እንደማያውቁት አጋልጠዋል። ይህ ብቻም ሳይሆን፥ የኢትዮጵያ ቴለቪዥን አቶ ጌቱ ሙሊሳን በአድራሻቸው አግኝቶ የሳቸውን አስተያየት ለመጠየቅ እንዳልተቻለ መናገሩ ፈጽሞ ሃሰት እንደሆነና፣ አዲስ አበባ እንደሚኖሩና አንድም ቀን ከፓርላማ ስብሰባ ቀርተው እንደማያውቁ ገልጸዋል። አቶ ጌቱ ጨምረውም፥ በአገዛዙ ካድሬዎች በተደበደቡበት ጊዜ የወንጀሉን መፈጸም ካሳወቋቸው የዜና አውታሮች አንዱ የኢትዮጵያ ቴሌቪዢን ራሱ መሆኑን ተናግረዋል።

በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገርናቸው አስተያየት ሰጪ፥ ወያኔ ውሸት መፍጠር የለመደው አሰራር መሆኑን ጠቅሰው፣ ብዙዎችን ወይ በገንዘብ እያባበለ ወይም እያስፈራራ ለሃሰት ምስክርነት እንደሚያቆም የታወቀ ነው ብለዋል። የቅንጅት አመራሮች በተፈበረከው “መንግስትን በሃይል የመናድ” ክስ ተከሰው ለይስሙላ ፍርድ ቤት በሚመላለሱበት ወቅት፣ አንድ የአቃቤ ህግ ምስክር ምንም እንደማያውቁ እና የሚናገሩትም አቃቤ ህጉ እንዲናገሩ ያዘዛቸውን መሆኑን በመግለጽ አገዛዙን ማዋረዳቸው ይታወሳል።

**(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)**

## የኢትዮጵያው አገዛዝ በህጋዊ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ በፍርድቤት ሽፋን የሚፈጽመውን ግፍ ቀጥሏል

የኢትዮጵያው አገዛዝ በህጋዊ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ ፍርድቤትን ሽፋን በማድረግ የሚፈጽመውን ግፍ ቀጥሏል። ባልተዘጋው የቀድሞው ቅንጅት ፋይል፥ በቅርቡ የጽኑ እስራት ፍርድ ከተላለፈባቸው 55 ተከሳቾች ውስጥ በስደት ላይ ያሉ የቅንጅት አደራጆች አንኳ እንዳልቀሩ ተዘገበ።

በሃይል የተቀለበሰውን የምርጫ 97 ውጤት ለማስመለስ በህዝቡ የተደረገውን ሰላማዊ ተቃውሞ ተከትሎ በህወሃት መራሹ መንግስት የተደረገው የማሰር፣ የመግደል እና ዜጎች እንዲሰደዱ ማድረግ አሁንም እንደቀጠለ ነው። የፖለቲካ ተቀናቃኞችን በፍርድ ስም ለማፈን ተብሎ በህወሃት የተቋቋመውና በኢህአዴግ አባላት የሚመራው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልዩ የሁለተኛ ወንጀል ችሎት ህዳር 8፣ 2001 ዓም በሰጠው ውሳኔ ከብዙ ግርፋትና ስቃይ በኋላ በአለም አቀፍ ግፊት ከእስር ተለቀው ከአገር በተሰደዱ የቀድሞ የቅንጅት አደራጆችን ጨምሮ በ55 ተከሳሾች ላይ የተለያየ የጽኑ እስራት ፍርድ ሰጥቷል።

ከአዲስ አበባ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አካባቢ ምንጮጫችን እና በስደት ከሚገኙ ተከሳሾች ባገኘነው መረጃ መሰረት የህወሃት ታማኝ ካድሬና የኢህአዴግ መንግስታዊ ልዩ ፍርድ ቤት 2ኛ ወንጀል ችሎት ዳኞች አደም ኢብራሂም፣ አሰፋ አብርሃ እና ዘሪሁን ቦዴ በተመሩት በሁለት የተለያዩ የወንጀል መዝገቦች የኮምፒወተር ቁጥር 55142 እና 55201 ፋይሎች እስከ 18 አመት ጽኑ እስራት ድረስ ፍርድ አስተላልፈዋል።

በስደት ሆነው ከተፈረደባቸው ውስጥ፡- የ23 ዓመቱ ወጣት ተማሪ እንዳልካቸው መለሰ አሳፈርከ፣ የ44 ዓመቱ ጎልማሳ መምህር አንተነህ ጌትነት ሙላት፣ አቶ አስከብር ገብሩ ታረቀ እና ወጣት ሚካኤል ጠና ጋሻው አበበ የሚባሉ ይገኙበታል።

ወያኔ በኢትዮጵያ ያለውን የፍርድ ሂደት ለአፈናው ማካሄጃ እንደሚጠቀምበት እና ይህንንም አሰራር የስልጣንን ወንበር ከተቆናጠጠበት ጊዜ ጀምሮ የህጋዊ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና መሪዎችን ለማፈን ሲጠቀምበት እንደቆየና አሁንም እንደቀጠለ ይታወቃል። ሰሞኑን ከሃገር ለመሰደድ የተገደዱት የአንድነት ለፍትህ እና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ብሔራዊ ምክር ቤት አባል አቶ አብዩ በለው ጉዳይ አገዛዙ በተፈበረኩ ክሶች የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ለእስር መዳረጉን እንደቀጠለ አሳይቷል።

አቶ አብዩ የቅንጅት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አባል የነበሩና የቅንጅት መሪዎች በእስር ላይ በነበሩበት ጊዜ ለተወሰነ ጊዜ ታስረው “መንግስትን በሃይል እና በህገ-ወጥ መንገድ ለመናድ” በሚለው የተፈበረከ ክስ ተከሰው ነበር። ከእስር ከተፈቱና የአንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ከተመሰረተ በኋላም የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት አባል እና የወጣቶች አደራጅ ሆነው በማገልገል ላይ ነበሩ።

ከጥቂት ወራት በፊት የወያኔ የደህንነት ሰራተኞች አቶ አብዩን የማሰርና የማስፈራራት ዘመቻ የጀመሩ ሲሆን፤ የሚነግሯቸውን ነገር ካልፈጸሙ ያንን ክስ መልሰው እንደሚያነሳሱባቸው አስጠንቅቀዋቸው ነበር። ይህ ክስ መልሶ እንዳይነሳባቸው ከፈለጉ በግልጽ አንድነት ፓርቲን በመልቀቅ ኢህአዴግን እንዲቀላቀሉ ትእዛዝ ተሰጣቸው። ይህንን ካልፈጸሙ ግን፥ ክሱ ተነሳስቶ እድሜ ልክ እስራት እንደሚፈረድባቸው፤ ካስፈለገም የግንቦት ሰባት አባል በመሆን እንደሚከሰሱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው እንደነበር አቶ አብዩ ለጀርመን ድምጽ ራድዮ በሰጡት ቃለ ምልልስ ገልጸዋል።

ባለፈው መጋቢት ወርም ፍርድ ቤት ተወስደው በ5000 ብር ዋስ ለመለቀቅ ችለው ነበር።

**(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)**

## ወያኔ እንኳንስ ከቆየው፤ ከቅርቡም ታሪክ አይማርም

«የግንቦት ሰባት የሽብር ሴራ እና የውጭ መገናኛ ብዙሃን ሽፋን» በሚል ርዕስ ሚያዝያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም. የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባዕዳንን ለማምታታት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ያወጣው ከራሱ ጋር የሚጣላው አስገራሚ መግለጫ ሚያዝያ 29 ቀን 1997 ዓ.ም.ን ያስታውሰናል፡፡ ሚያዝያ 29 ቀን 1997 ዓ.ም. በመደለልም በማስገደድም ያሰባበበው በርከት ያለ ሕዝብ መስቀል አደባባይ በመውጣቱ የፈነደቀው የወያኔው ሹም ህላዊ ዮሴፍ በምሽቱ የቴሌቪዥን እወጃ በተሽከርካሪ ወንበር እየተለጠጠ «ተቃዋሚዎች አዲስ አበባ ውስጥ አንዳችም ደጋፊ እንደሌላቸው አሳይተናል» በማለት ተንቀባረረ፡ ይኼ ጉራ ግን ብዙ አልዘለቀም፤ የማግስቱ ሚያዝያ 30 ማዕበል ጠራርጎት ጠፋ።

ይህ በሆነ ልክ በአራተኛ ዓመቱ ሚያዝያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም. የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያወጣው መግለጫ "ግንቦት 7 የተባለው ድርጅት በአገር ውስጥ አንዳችም ደጋፊ የሌለው፤ ጥቂት የሆኑት አባላቱ በሙሉ ያሉት በውጭ አገራት ውስጥ ነው" ካለ በኋላ ይኼ ምንም አባላት የሌሉት ድርጅት ሊያደርስ ስለነበረው ጥቃት ይዘረዝራል፡፡ ይኼ የሚያሳየን ወያኔ በአራት ዓመታት ውስጥ አንዳችም ጠቃሚ ትምህርት አለመውሰዱን ብቻ ሳይሆን መማር የሚችል የረባ አእምሮ ያለውም ሰው ከመካከላቸው እንደሌለ ጭምርም ነው፡፡

መግለጫውን የፃፈው ሰው ያሳሰበው ጉዳይ እሱ "ሽብር" ያለውን ተግባር በዓለም ዓቀፍ ሚዲያዎች "የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ" ተብሎ መዘገቡና የግንቦት 7 መሪዎች የሚዲያ ሽፋን ማግኘታቸው ስለነበር፤ "ግንቦት 7 አገር ውስጥ አባላት የሉትም" እና "ግንቦት 7 የሽብር ጥቃት ሊያደርስ ሲል ደረስንበት" በሚሉ ሃረጎች መካከል ያለውን ጉልህ ተቃርኖ ሊገነዘብ አቅሙ አልፈቀደለትም፡፡ በዚህም ጸሃፊው የራሱን የድንቁርና ጥልቀት ለዓለም ፍንትው አድርጎ አሳይቷል። በነገራችን ላይ የመፈንቅለ-መንግስቱንም ዜና ያሰራጩት እነሱው መሆናቸዉ ልብ ይሏል፡፡ ወያኔ ሆይ፤ የሩቁ እንኳን ባይቻልህ የቅርቡን ታሪክ አስታውስ!!! ሚያዝያ 29 1997ን ተከትለው የመጡት ሚያዝያ 30 እና ግንቦት 7 መሆናቸውን አትዘንጋ!!!

የተምታታዉ መግለጫ "ምዕራባዊያን የዜና አዉታሮች "የሽብር ጥቃቱን" "የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ" ያሉት ጥቂት በሥራ ላይ ያሉ የጦር መኮንኖች በሴራዉ ተሳታፊ ስለሆኑና ምዕራባዊያን በአፍሪካ ዉስጥ መንግሥት በአብዛኛው የሚለወጠዉ በሽብር እንጂ በምርጫ ሣጥን አይደለም ብለው እስካሁን ስለሚያምኑ ነው" ሲል ግምቱን አስፍሯል፡፡ ይኼ የወያኔን ድንቁርና በሚገባ የሚገልፅ አባባል ነው፡፡ *በአፍሪካ ውስጥ መንግሥት የሚለወጠው በአብዛኛው በሽብር እንጂ በምርጫ ሣጥን አይደለም* በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ምን ውሸት አለበት? ስለሌሎች ትተን አገራችን ላይ ብቻ ብናተኩር ኢትዮጵያ ውስጥ በምርጫ መንግሥት ተቀይሮ ያውቃልን? በሰላም ለመቀየር የተደረገውንም የ1997 ብቸኛ የምርጫ ሙከራ ራሱ ወያኔ በሽብር አጨናግፎ ህገወጥ በሆነ መንገድ ስልጣኑ ላይ ቂብ እንዳለ አልቀረምን?

መግለጫው ቀጥሎ ደግሞ "በኢትዮጵያ ያለው የፌደራል አወቃቀር ሥልጣን ወደ ክልሎች በመውረዱ መፈንቅለ-መንግሥት የማይሞከር ተግባር አድርጎታል" ይለናል፡፡ የወያኔ ፌደራሊዝም የስም ብቻ መሆኑ ሁሉም የሚያውቀው ጉዳይ ነው፡፡ በፌደራል አወቃቀር መፈንቅለ-መንግሥት "የማይሞከር ነው" ብሎ ያስተማራቸው ማን እንደሆነ ለጊዜው አላወቅነውም፡፡ አባባሉ ግን ከዚህ ክርክር የበለጠ ዋጋ ያለው መልዕክት ይዟል፡፡ ለምንድነው ወያኔ በዘውግ የተደራጁ ክልሎችን የፈጠረው? እነሆ ሳያስበው በዚህ መግለጫው የልቡን አወጣው !!!

የክልሎች ባለሥልጣናት ይህ ባጋጣሚ ብቅ ያለችው መልዕክት ይድረሳችሁ!!! ወያኔ እናንተን የሚፈልጋችሁ፤ የእናንተ መኖር በተለያየ መልኩ "ማዕከላዊ ስልጣኔን ለመከላከል ያመቸኛል" ብሎ ስላመነ ነው፡፡ በዋንኛነት ወያኔ የሚፈልገው ከማዕከል እየጋጠ በሚጥለው ባዶ ቅልጥም ላይ በየክልላችሁ ስትናከሱ የሃገር ሃብትንና ሰልጣንን በመቆጣጠር ያለምንም ተቀናቃኝ ለዘላለሙ ለመኖር ነው፡፡ በሌላ መልኩም "ድንገት ማዕከላዊ ሥልጣኔ ከተናጋብኝ ወደ ክልሎች ወርጄ እከላከላለሁ" የሚል እምነት ወያኔ እንዳለው የሚያሳይ ነው፡፡ ለዚህም ነው ስም ብቻ ሰጥቷችሁ እየሸነገለ የሚጫወትባችሁ፡፡ ወያኔ የክልሎች ነዋሪዎች ኢትዮጵያዊያን መሆናቸውን፤ እዚያም ግንቦት ሰባት መኖሩን ጭራሽ አላገናዘበም፡፡ በክልል ተቋማት ውስጥ በማናቸውም ደረጃ ላይ ለምትሰሩ ወገኖች በዚህ ዓረፍተ-ነገር ውስጥ ያለው "ትዕቢትና ንቀት ጎልቶ ይሰማችሁ፡፡ ውርደት በቃን ልትሉ ይገባል" እንላለን፡፡

ጉደኛው መግለጫ ወያኔ "ሕጋዊ" መንግሥት ስለሆነ "በተገኘዉ አማራጭ ሁሉ እንፋለመዋለን" ለሚሉ ወገኖች የሚዲያ ሽፋን እንዳይሰጡ የአሜሪካንና የብሪታኒያን መንግሥታት ተማፅኗል፡፡ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ ወያኔ ህገወጥ፣ ዘረኛና ህዝብን በጅምላ የሚጨፈጭፍ ጨቋኝና ዘራፊ አገዛዝ ስለሆነ ይህንን አገዛዝ አስወግደን በምትኩ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የምናደርገውን ትግል ደግፉ እያሉ ይጠይቃሉ፡፡ የማንን ተማፅኖ ነው መስማት ያለባቸው?

ዲሞክሲያዊ አገራት የሚመሩባቸዉ እሴቶች አምባነኖችን ለመፋለም ከተነሱ የዲሞክራሲ ኃይሎች ጎን እንዲቆሙ ያደርጋቸዋል ብለን እናምናለን፡፡ ስለሆነም ታላቋ ብርታኒያ፣ ዩ ኤስ አሜሪካ እና ሌሎችም ዲሞክራሲያዊ አገሮች መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ በዘር ማጥፋትና ጅምላ ጭፍጨፋ ወንጀሎች ለዓለም ዓቀፍ ፍርድ እንዲቀርቡ፤ ለነፃነታችንና ለአገራችን የምናደርገዉን ትግል እንዲደግፉ አበክረን እንጠይቃለን፡፡ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣የሂዩማን ራይትስ ዎች፣ የጀኖሳይድ ዎችና ሌሎችን ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች በወያኔ መዳፍ በመሰቃየት ላይ ካለው ወገናችን ጎን በመቆማችሁ ያለንን አክብሮት እየገለፅን ድጋፋችሁን በተጠናከረና በተደራጀ መንገድ እንድትቀጥሉ በአፈና ሥር ባለው ወገናችን ስም እንጠይቃለን፡፡

በመጨረሻም ለሰሞኑ የወያኔ መደናበር ምክንያት የሆናችሁ፤ በወያኔ ሠራዊት ውስጥ ያለውን በዘረኝነት የተተበተበውን የስለላ መረብ በጣጥሳችሁ እምቢተኝነታችሁን በማሳየት ወያኔን ላርበደበዳችሁና ለማይበርደው የነጻነት ትግል የድርሻችሁን ላበረከታችሁ ወገኖቻችን ያለንን የላቀ አክብሮት እንገልፃለን፡፡ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ከጎናችሁ መቆሙን፣ እየከፈላችሁት ያለው መስዋዕትነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ፍሬ የሚያፈራ መሆኑን ልናረጋግጥላችሁ እንወዳለን፡፡



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## “ሰላማዊና ሰላማዊ ትግል ብቻ!” ለማደናገሪያነት ሲውል

ከዝግጅት ክፍላችን

ወያኔ በመንግሥት በጀት የሚያስተዳድራቸው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬድዮ፣ አዲስ ዘመንና ሄራልድ ጋዜጦች ለፕሮፖጋንዳው አይበቁትም፡፡ እንደ «ሪፓርተር» አይነቱ በነጻው ፕሬስ ስም የሚነግድ፣ አልጋ ሲረጋጋ ተቃዋሚ እየመሰለ የሚያደናግርና ወያኔ ችግር ሲደርስበት «አለሁልህ» የሚለው ልሳን አለው፡፡ በእዚህም ላይ እንደ «አይጋ ፎረም» ዓይነቱ ልቅና ዘረኛ ድረ-ገፅንም አሰማርቶአል፡፡

ሰሞኑን እነዚሁ ከላይ የጠቀስናቸው ነውረኛ የወያኔ ልሳኖች (ሪፖርተርና አይጋ ፎረም) ስለ “ሰላማዊ ትግል” ሊያስተምሩን ቆርጠው ተነስተዋል፡፡ በቅድሚያ በአዕምሮዓችን የሚመጣው ጥያቄ «የት ስለሚያውቁት ሰላማዊ ትግል ነው ሊያስተምሩን የሚዳዳቸው?» የሚለው ነው፡፡ እነሱ ስለ ሰላማዊ ትግል በማላዘን በጆሮ ጠገብ ደረጃ (በስሚ ስሚ) የሚያውቁትን ይህንን ቃል ከሰሞኑ የሙጥኝ ብሎ መወትወት ያስፈለጋቸው አላማው ግልጽ ነው፡፡ ይኸዉም ከወትሮው በእጅጉ ለየት እና መረር ያለ ቀውስ በወያኔ ዘረኛና መርዘኛ አገዛዝ ላይ በመደቀኑ ነው። ቀውሱ ለየት ያለ ነው ያልንበት ምክንያትም የወያኔ ለከት ያጣ ያፈና አገዛዝ ስርአት፤ ኢፍትሃዊነት፤ አድሎአዊነትና ዘረኝነት ያንገፈገፋቸው ዜጎች አሻፈረኝ ከዚህ በሁዋላ ከባርነት ሞትን እንመርጣለን ማለታቸው የስርአቱን ቁንጮዎች እንቅልፍ ስለነሳቸው ነው። የሰሞኑን ሰላማዊ ትግል የሚሉትን የወያኔ ከንቱ ውትወታ አስቂኝና አስገራሚ የሚያደርገው አፋኙ አገዛዝ ራሱ ያፈናው ሰለባ የሆኑትን ዜጎች ሰላማዊ በሆነ መንገድ ታገሉኝ ብሎ መምከሩ ነው፡፡ቋንቋው ሰላማዊ ትግል የሚለው ይሁን እንጂ ወያኔ በነሪፖርተር በኩል ለማስተላፍ የፈለገው መልእክት ይሉኝታ የሌለው የጥጋበኛ መልእክት ነው፡፡ ወያኔ እያለ ያለው «ተቃዋሚዎች የትግላቸሁን አይነት፤ ወርዱና ቁመቱ፤ መልኩና ይዘቱ እንዲሁም አመቺው ጊዜና ቦታም እኔ ወያኔ ልወስንላችሁና ተቃዋሚ የሚል ስም ሰጥቼ አጃቢ ላድርጋችሁ» ነው፡፡ ወያኔ መሳሪያወን አስቀምጦ፤ እንዳሻው ጠፍጥፎ የሰራቸውን፣ የምርጫ ቦርድ፣ የፍትህ ስርአቶች፣ እንዳሻው የሚያናፋበትን የመገኛኛ ብዙሃን ገለልተኛ አድርጎ በሰላም ሊገጥማችሁ ይገባል፡፡ እናንተም ለአንዲህ አይነቱ የሰላም ጥሪ መልስ ስጡ የሚል አይደለም፡፡

ልብ በሉ ሪፖርተር ለዚሁ ዉትወታው የሙጋቤን መንግስት በማጣቀሻነትም አለቦታው አንስቶአል፡፡ የወያኔ አፈቀላጤ ያልገባው ነገር ቢኖር የመለስ ዜናዊ አምባገነናዊና ዘረኛ ስርአት ከዚምባቤ ጋር የሚያመሳስለው ነገር በጣም ትንሽ መሆኑን ነው፡፡ መለስ ዜናዊ ሪፖርተር በምሳሌነት የጠቀሰውን የሙጋቤን ሩብ ያህል እንኳን ለአገር ዘላቂ ጥቅም የመቆርቆር ፈቃደኝት ቢኖረዉ ኖሮ በምርጫ 97 ማግሥት ቅንጅት ያቀረበለትን የአብረን እንሥራ ልመና በትዕቢት ባልገፈተረውም ነበር፡፡ ወያኔን «ባታሸንፍም ስልጣኑን በሙሉ ጠቅልለህ ያዘው፤ ብቻ የራስህን ህገ-መንግሥት አክብርልን፤ አብረን ዲሞክራሲያዊ ተቋማትን እንገንባ» ብሎ ከመለምንና በማስለመን ባለፈ ቅንጅት ምን ማድረግ ይችል ነበር? ቻንግራይ ይኸን ያህል ሂደዋልን? ተበዳይን መወንጀል የለመደዉ ሪፖርተር ይባስ ብሎ ወያኔ የጦርነት ልምድ ያለውና የማይደፈር አድርጎ በማቅረብ ሊያስፈራራን ይሻል፡፡

የወያኔን የጦርነት ችሎታማ በሱማሊያ ውስጥ አየነው እኮ፡፡ ለነጻነቱ የሚዋጋን ጥቂት ኃይል ማሸነፍ አቅቶት፣ የፈረደበትን የደሃ ወታደር ወገናችንን ሬሳ በባእድ ሀገር እንደ አልባሌ ነገር በትኖ ተዋርዶና ጭራውን ቆልፎ በሽሽት አልወጣም እንዴ? ወያኔ የረሳውና የደርግን ውድቀት ያፋጠነው፣ ደርግ በህዝብ ላይ በፈጸመው ወንጀል ምክንያት ከሕዝብ ስለተነጠለና ስለተጠላ ብሎም ድጋፍ ስላጣ ነው፡፡ ይህ ባይን ኖሮ ወያኔ አዲስ አበባ መግባት ቀርቶ ከደደቢት ዋሻ ብቅ ማለት አይችልም ነበር፡፡ ዛሬ ወያኔ በሀገር ከሃዲነቱና በዘረኛነቱ፤ በንፁሃን ዜጎች ጨፍጫፊነቱና በዘራፊነቱ ከደርግ በላይ የተጠላ ሆኗል፡፡ ወያኔን ለማስወገድ ቆርጦ የሚነሳ ኃይል እንደ ህወሃት ከሰሜን ጫፍ ከአንዲት ደደቢት ከምትባል ጥግ ተነስቶ ወደ አዲስ አባባ 17 አመት ሙሉ መንፏቀቅ የለበትም፡፡ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ ስለሚኖረው በየትኛውም የአገሪቱ ክልል መጀመር ይችላል፡፡ «እኔ ግንቦት 7 ነኝ፣ የነጻነት መንፈስ፣ ሁሉም ቦታ የምገኝ ብለው የግንቦት 7 ደጋፊዎች የሚናገሩት የጸረ ወያኔ ምሬት ሃገሪቱን የሸፈናት መሆኑን ስለሚያውቁ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ የነጻነት ጥማት የሃገሪቱ ዜጎች በሚያቃጥልብት ሁኔታ የወያኔ የጦር ልምድም ሆነ የመሳሪያ ብዛት ከሽንፈት አያድነውም፡፡ ወያኔ ጀግና ነው ብለው የሚያስቡ ከሆነ ሪፖርተር፣ አይጋ ፎረም፣ የኢትዮጵያ/የወያኔ ቴሌቪዥንና ራድዮ ምን አስጨነቃቸው? ምነዉ እንደ ጌታቸው እንደ መለስ ዜናዊ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላቸሁ አላሉንም? በግልባጩ ግንቦት ሰባት ለወያኔ «ጀግና ነኝ የምትል ከሆነ መንገዱን ጨርቅ ያድርግልህ» ብሎታል፡፡ ሰላማዊ ትግል የሚዋጣው ለወያኔ እንጂ የመላው ኢትዮጵያን ሕዝብ ድጋፍ በቀላሉ ለሚያገኘው ጸረ-ወያኔ ታጋይና አታጋይ አይደለም፡፡

ወያኔ ስለሰላም እየዘመረ የሰላምን እርግብ ተኩሶ የገደለ አረመኔ ነዉ፡፡ በግንቦት ሰባት እምነት ከወያኔ ጋር «ሰላማዊና ሰላማዊ ትግል ብቻ!» ብሎ ጫወታ ዉጤቱ የወያኔን የሥልጣን፤ የኢትዮጵያችንና የታጋዮቻችንን መከራ ማርዘም ነዉ፡፡ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ አቶ መላኩ ተፈራ እና ሌሎችም በርካታ ሰላማዊ ታጋዮችን አስሮ፣ ወያኔ እንደ እርኩስ ሲያወግዘቸው የነበሩትን አቶ ኃይሉ ሻውልንና መኢአድን የሰላማዊ ታጋይ ተምሳሌት አድርጎ በቴሌቪዝን ማቅረብና በአይጋ ፎረም መለጠፉ የጨነቀው እርጉዝ ያገባል የሚያሰኝ ነው፡፡ መቼም ወያኔ ለመኢአድ ካለው ፍቅር ይህን እንደማያደርግ እናውቃለን፡፡ ወይስ የወያኔ ተቃዋሚዎች መኢአድ በወያኔው ቴሌቪዥን ተወደሰ ብለን ትግላችንን ከወያኔ ጋር ማድረጋችን ቀርቶ በመኢአድ ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረን ታስቦ ይሆን? የወያኔ የሰው መመዘኛ የራሱ ድንቁርና ነውና ግንቦት ሰባት በእንዲህ አይነቱ የሞኝ ወጥመድ ውስጥ ይወድቃል ብሎ ማሰቡ የራሱን ጅላጅልነት የሚሳይ ነው፡፡

የግንቦት ሰባት የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዓላማ የኢትዮጵያ ሕዝብ የፈለገውን በነፃነትና በሰላም መርጦ ለመሾም፤ ያልፈለገውን ደግሞ እንደዚሁ በነፃነትና በሰላም ለመሻር የሚያስችለውን ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሥርዓት በወያኔ አገዛዝ ሥር ሊገነባ አይችልም፡፡ ወያኔ ለዚህ ፍጥረቱም አይፈቅድለትም ብቃቱም የለውም፡፡

በነፃና ፍትሃዊ ውድድር ወያኔ ቢያሸንፍ ግንቦት ሰባት ደስተኛ ነው፡፡ ወያኔ ድፍረት አግኝቶ ራሱን ተፎካካሪም፣ ድምፅ ቆጣሪም፣ ዳኛም መሆኑ ማስቀረት በሚቻልበት መንገድ ይደራደር እንላለን፡፡ ወያኔ እራሱን ማዳን የሚችልበት ሰላማዊ አማራጭ ይህ ብቻ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ወያኔም ሆነ ኢህአዴግ እንደ ፓርቲ የመቀጠላቸውን እድል እንኳን ሊያጡት ይችላሉ፡፡

ወያኔ በሰላማዊ መንገድ ብቻ ሽንፈትን ይቀበላል ብሎ ግንቦት ሰባት አያምንም፤ ስለሆነም ከሰላማዊ ትግል በተጨማሪ ሌሎችንም የትግል አማራጮችን የመፈተሽ እስትራቴጂ ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ሰላማዊ ትግል ስንልም የመለስ ዜናዊን ፈቃድ የሚጠይቅ፣ ወያኔ ራሱ የማያከብረውን ሕገ መንግስት የሚያጣቅስ አይደለም፡፡ ግንቦት ሰባት በመረጠውና የወሰነውን የሰላማዊ የትግል ስልት በስራ ላይ እናውላለን ማለታችን ነው፡፡

የሪፖርተር፣ የአይጋና የሌሎችም የወያኔ ደላሎች የሰሞኑ የሰላማዊ ትግል ጥሪ ደወል የተደወለው ለተቃዋሚዎች በመቆርቆር ይምሰል እንጂ ወያኔን ለማስወገድ ሊፈጠር የሚችለውን የአመጽ ማዕበል በመፍራት የተሰነዘረ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በአንድ ወቅት «ጦርነት የመሥራት ችሎታቸዉን» እያደነቁ በከፍተኛ ኩራት ሲናገሩ የነበሩ የቀድሞ የወያኔ የጦር አዛዥ ሁኔታውን መርምረው ለቀድሞ ጓደኞቻቸው «እረ እባካችሁ ይህ የእብሪት ጎዳና የትም አያደርሳችሁም፣ የተቀመጣችሁበት እሳተ ገሞራ ፈንድቶ ሊለበልባችሁ በመንተክተክ ላይ ነው» የሚል ምክራቸውን ለግሰዋቸዋል፡፡ እዕምሮ ቢኖራቸው የወያኔ መገናኛ ብዙሀን ገዡዎች የአቶ ስየ አብርሃን ማስጠንቀቂያ ሰምተው ምክራቸውን ለተቃዋሚ ኃይሎች በተለይ ለግንቦት ሰባት ሳይሆን ለራሱ ለወያኔ ባደረጉት ነበር፡፡

*«ወያኔ ሆይ! ከአንተም በላይ ሠራዊት፣ ከአንተም በላይ መሣሪያ የነበራቸው ነበሩ፡፡ ይህ ግን ከጥፋት እንዳላዳናቸው ለማወቅ የአልባኒያን፣ የሩማንያንና የሌሎችንም የዓለም ዳርቻዎች ገዢ መደቦች ታሪክ ማሰስ የለብህም፡፡ መለስ የተቀመጠበት ዙፋን ላይ የፀሐዩ ንጉስና ሥዩመ እግዚአብሄር ይባሉ የነበሩት አጼ ኃይለ ሥላሴ፣ ቀጥሎ ደግሞ ቆራጡና አብዮታዊው መሪ ተብለዉ ይሞካሹ የነበሩት ኮለኔል መንግስቱ ኃለማርያም ተቀምጠውበት ነበር፡፡ የሁለቱንም መጨረሻ እንዴት እንደነበር ታውቃለህ፡፡ የገደልኩትን ገድዬ የዘርፍኩትን ዘርፌ ሌላ ሃገር እሄዳለሁ እንዳትል ዓለም ተቀይሯል፡፡ ሸሽቶ የተዘረፈን ገንዘብ በሰላም እያላመጡ የሚያረጁበት ዓለም ከጠፋ ሰንብቷል፡፡ በጣት በሚቆጠሩ ዘረኞች ድጋፍ ላይ ተንጠልጥዬ በመሣሪያ ኃይል ለዘላለሙ እገዛለሁ የሚለው ህልምህ ሳይወለድ የሞተ፣ ሳይዘራ የረገፈ እንደሆነ እወቀው!!! ጦርነት መሥራት አውቅበታለሁ የሚለው በሱማሊያ የተነፈሰውን ጉራህን ወደ ጎን አድርግህ ቀኑ ሳይመሽ በቀና ልቦና ሰላማዊና የሰለጠነ ፖለቲካ ሂደት ለማስጀመር ከተቃዋሚዎች ጋር ጉባኤ ተቀመጥ፡፡»*

ሊባል ይገባዋል፤ ወያኔ፡፡

በመጨረሻም ይህ የወያኔ ራድዮና ቴሌቪዥን፣ የሪፖርተርና የአይጋ ድረ-ገጽ የሰላማዊ ትግል ጥሩነት ማደናገሪያ ያነጣጠረው በሰላማዊ ትግል ብቻ ለውጥ ይመጣል ብላችሁ ተስፋ በምታደርጉ ወገኖቻችን ላይ ከሆነ፣ ለእነዚህ ወገኖቻችንን አንድ ወገናዊ ምክር አለን፡፡ «የተቀናቃኛችሁን ባህሪይ ደጋግማችሁ መረምሩ፡፡ ወያኔ ምርጫን የሚፈልገዉ «ማሸነፉን» ለማብሰሪያነት ብቻ ነዉ፡፡- ለዚህ መሣሪያ የመሆን መብታችሁን ግን እናከብራለን፡፡

ለውጥ ፈላጊ የሆንከው ኢትዮጵያዊ ግን መንገዱን ጨርቅ ያድርገልህ የሚል የእብሪት አባባል ካደመጥክበት የወያኔ አፍ «ሰላማዊና ሰላማዊ ትግል ብቻ» የሚሉ ማደናገሪያዎች ስትሰማ «ምነው በባዶ እጃቸውን የተሰለፉትን የልጆቼን፣ የአህቶቼንና ወንድሞቼን የእናትና የአባቶቼን ደም ስታፈስ ያልታየህ የሰላማዊነት ውበት ዛሬ እንዴት ተገለጠልህ» በማለት ወያኔን ልትጠይቀው ይገባል፡፡ በመለስ ዜናዊ ተራ ብልጣ ብልጥነት ታዘው ስለሰላማዊ ትግል ጥሩነት መግለጫ ሰጪ ለሆኑትን የወያኔ መገኛና ብዙሃን የቀበሮ ጩኸት ቁብ ሳትሰጥ፣ ግንቦት ሰባት ለቀየሰዉ ሁለገብ ትግል ራስህ አዘጋጅ፡፡ በህብረት ከተነሳን፣ ወያኔ ወደደውም ጠላውም፣ የሃገራችን የመብታችን የእጣችን ባለቤት መሆኛችን ቀን ቅርብ ነው፡፡

## በመደናበር ላይ መደናበር

ጽናት ፍቅሩ

ከሁለት አመት በፊት አንድ የቀድሞ የአሜሪካ ዲፕሎማት ቃሊቲ እስር ቤት መጥተው እንዲህ ብለውን ነበር፤ "እኔ፣ አቶ መለስ፣ አቶ በረከትና አቶ ስብሀት ሆነን በእናንተ ጉዳይ ላይ ሰፊ ውይይት አድርገናል። ሰዎቹ እንደነገሩኝ ከሆነ 'በጥቅምቱ የ1998 ዓም ህዝባዊ ተቃውሞ ወቅት ስልጣናቸውን ለማጣት ተቃርበው ነበር። አሁንም የጥቅምቱ አመጽ ከፈጠረባቸው ድንጋጤ ገና የወጡ አይመስለኝም።እባካችሁ ለእነዚህ ሰዎች ከእንግዲህ አመጽ እንደማይነሳ ዋስትና ስጧቸውና ከዚህ እስርቤት በሰላም ውጡ።'"

ሌላ የአውሮፓ ዲፕሎማት ደግሞ መጥተው እንዲህ አሉን፤ "እኛ እናንተን ለማስፈታት ስንል በመንግስት ላይ ማእቀብ መጣል አልጠፋንም፤ ነገር ግን እንዲህ ብናደርግ የሚጎዳው ደሀው ነው። በእውነት እያዘንኩ የምናገረው ላገርና ለህዝብ የሚያስብ መንግስት እንደሌላችሁ ነው። መሪዎቻችሁ የሚጨነቁት ስለስልጣናቸው እንጂ ለአገር አይደለም። የአንድ አገር መሪ ሆኖ የተቀመጠ ሰው፣ ለአገሩ ጠላት ሲሆን ሳይ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው። መንግስታችሁ ለህዝብ ደንታ የሌለው መንግስት ነው። በጣም አዝናለሁ።" የሰሞኑ የወያኔ መደናበር የዲፕሎማቶቹን ንግግር አስታወሰኝ።

ከግንቦት 97 ምርጫ በሁዋላ የወያኔ መሪዎች ቅዠት ውስጥ መግባታቸው ተብሎ ያለቀለት ነገር ነው። ለቅዠታቸው ማስታገሻም ይሆን ዘንድ ያልወሰዱት የኪኒን አይነት አልነበረም። በመጀመሪያ የቅንጅት መሪዎችን፣ ጋዜጠኞችንና የሲቪክ ማህበር አባላትን እና የአይኑ ቀለም ያላማረውን ሁሉ እየሰበሰቡ ዘብጥያ ላኩት። ይህ ግን ሌላ ችግር ይዞ መጣ። በአለም ላይ ያልተጠበቀ ውግዘትን አስከተለ። የወያኔ እውነተኛ ባህሪም ለጸሀይ ተጋለጠ። ይህንኑ ለመሸፋፈን ደግሞ የሶማሊያን ጦርነት ፈጠሩ። ለጊዜውም ቢሆን የአሜሪካን ድጋፍ አገኙ። እያደር ግን ሶማሊያ እንኳን ሊሸነፍ እንደ ጠጅ እየጠነከረ መጣና የወያኔን ሰራዊት ወጥ በወጥ አደረገው። ወያኔም በፉከራና በሽለላ እንዳልገባ ሁሉ እንደሌባ ሾልኮ ወጣ። ከዚያም የሸንፈቶቹ ሁሉ ማስረሻ የሚሆን አጋጣሚ አገኘ- "ሚሊኒየም" ። ሚሊኒየሙም ቢሆን ግን የወያኔን የተኩላ ባህሪ ከማጋለጥ ውጭ ምንም ሳይፈይድ አመለጠ።በእውቅና እጦት የሚሰቃዩት የወያኔ መሪዎች ግን አሁንም ድራማ ከመስራት አላረፉም።ትኩረት ይይዝልናል ብለው ያሰቡትን የኢኮኖሚ እድገት ድራማ ሰርተው አቀረቡ። "ኢኮኖሚያችን በአጭር ጊዜ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ይሰለፋል" የሚል ተረት ተረት አስነገሩ። እንደታሰበው ሳይሆን ቀረና ሳይውሉ ሳያድሩ " እርዳታ ካላደረጋችሁልን ልንበታተን ነው"" በሚል ሰበብ ልመና አቀረቡ።

ከወራት በፊት ደግሞ ካልጠበቁት ስፍራ እጅግ አስጨናቂ ወሬ ደረሳቸው። ሂውማን ራይትስ ወች የተባለው ድርጅት ጦራችሁ በኦጋዴንና በሶማሊያ የጦር ወንጀል ፈጽሟል ብሎ ሹክ አላቸው። ይህ በተነገራቸው በወሩ ደግሞ "ጀኖሳይድ ወች" የተባለው ድርጅት " በዘር ማጥፋትና በሰውልጆች ላይ በተፈጸመ ግፍ ልትከሰሱ ትችላላችሁ" አላቸው። ወዳጅ የሚሉት የአሜሪካ መንግስትም፣ እንዲያ እንዳልደሙለትና እንዳልሞቱለት፣ ሰብአዊ መብት በገፍ የጣሱበትን መረጃ ይፋ አደረገ። በቃ የወያኔ መደናበር ልኩን አጣ። ነገሩ ሁሉ በዚህ ሲሰፋ በዚያ መቀደድ ሆነ ። ወያኔ በቴሌቪዥን ቢያስነግር መግለጫ ቢያወጣ ማንስ ሊሰማው። ደግሞ "የሶማሌያ መንግስት ግንቦት 7ትን አወገዘ" የሚል ዜና አንብቤ በሳቅ ተተረተርኩ። የባሶና ወረዳ አርሶ አደሮች የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አስጠነቀቁ የሚለው ዜና ትዝ አለኝ። አይ መደናበር ደጉ።

ሰሞኑን የተሰማው ደግሞ ወያኔን ከማደናበር አልፎ ልብሱን ጥሎ እንዲሄድ የሚያደርገው ነው።ታስታውሱ ከሆነ፣ ከአመት በፊት የቀድሞ የቅንጅት፣ አሁን የግንቦት 7 መሪዎች፣ ካገር ሲሰደዱ ወያኔዎችና ደጋፊዎቻቸው ከመፈንደቅ አልፈው በሀይል ተሳልቀው ነበር።ለምሳሌ አቶ ልደቱ አያሌው "ዶክተር ብርሀኑ ሁለገብ ትግል እናደርጋለን እያሉ ነው እርስዎ ይህን እንዴት ይመለከቱታል ተብለው በጋዜጠኛ ሲጠየቁ " የብርሀኑ ነጋ ውጊያ የጨበጣ ነው።ብርሀኑ ነጋ ወደ አገሩ ላለመግባት ለህዝቡ ያቀረበው ምክንያታዊ ስልት ነው" የሚል መልስ ሰጥተው ነበር።

ኢትዮቻናል የተባለ የአንድ አጭበርባሪ የማስታወቂያ ሰራተኛ ድህረገጽ ደግሞ በዜና መክፈቻው ላይ ሁሉ የዶ/ር ብርሀኑን ስም ካልተጨመረበት ጌቶቹን ያስደሰተ አይመስለውም ነበር። ለምሳሌ ግንቦት 7 የገንዘብ መዋጮ በጠየቀበት ጊዜ ድህረገጹ እንዲህ ብሎ ነበር ፤"ይሄኔ የግንቦት ሰባት ሀላፊዎች በውጭ ያለውን ኢትዮጵያዊ ቁጥር በ 500 ዶላር አባዝተው በሚሊየነርነት ህልም እየዳከሩ ይሆናል።"

ዛሬ ያሁሉ ተለውጠ። እነልደቱ ድምጻቸውን ማጥፋት ብቻ ሳይሆን፣ ኢህአዴግ እነሱን ሳያማክር መግለጫ በማውጣቱ ተበሳጭተው "በአላዋቂ ፕሮፓጋንዳ እነብርሀኑን ጀግና አደረጋችሁዋቸው" ብለው አኩርፈዋል አሉ። እነ ኢትዮቻናል ባንዴ ተገልብጠው እነ ብርሀኑን ከዘራፊነትና ከፈሪነት ተርታ አንስተው የአሸባሪነት ማእረግ ሰጧቸው። ሳያውቁት ብርሀኑንና ቢን ላደንን ጎን ለጎን አስቀምጠው ብርሀኑን አለማቀፍ ጀግና አሰኙት። ለነገሩ እነብርሀኑ አሸባሪ ቢባሉ የሚደሰቱበት እንጂ የሚቆጩበት አይመስለኝም። ማንዴላም አሸባሪ ተብሎ ተፈርጆ ነበር። ዛሬ አሜሪካ ስትይዘው ቃሉ ክብሩን አጣ እንጅ፣ "አሸባሪ" የሚለው ቃል እኮ አባቶቻችን ለጀግንነት መግለጫ ይጠቀሙበት የነበር ቃል ነው። አጼ ቴዎድሮስ፣ በላይ ዘለቀ፣ አበበ አረጋይና ብዙ ስመጥር ጀግኖች ጠላትን በማሸበራቸው የልጅ ልጆቻቸው "አሸብር ቴዎድሮስ፣ አሸብር ዘለቀ" እየተባሉ ይጠራሉ። "አሸብር" የሚባል የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጋዜጠኛም አለ ልበል? እርሱም ቢሆን በዜናው ሰውን ስለሚያሸብር አይናቅም። በግንቦት የተወለዱ ህጻናት ከእንግዲህ "አሸብር ብርሀኑ" ፤ "አሸብር አንዳርጌ" እየተባሉ ቢሰየሙ እንዳይገርማችሁ።

ወያኔ አሁንም መደናበሩን ቀጥሏል። በቅርብ ጊዜ የፈጠረው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ድራማ፣ በሳምንት ውስጥ ለውጦ የነፍስ ግድያ ድራማ አድርጎ ቢሰራውም መደናበሩን ከማጉላት ውጭ ምንም አልፈየደለትም። የወያኔ የቅርብ ጊዜ መደናበር ምክንያቱ ስልጣንን ከማጣት ጋር ብቻ የተያያዘ እንዳይመስላችሁ። ይልቁንስ በሱዳን ፕሬዝዳንት ላይ የደረሰው እንዳይደርስበት ወያኔ ተጨንቋል። ከእንግዲህ የወያኔ እጆች በየትኛውም የአረብ ወይም የፈረንሳይ ሽቶዎች ቢጠረጉ ደም ደም መሽተታቸውን አያቆሙም። እነዚህም እጆች ተይዘው እኔ ወደ ምኖርባት የኔዘርላንድስ ከተማ ወደ ሆነችው ዘሄግ (ደነህህ) መምጣታቸው አይቀርም። ያን ጊዜ ምግብ ማን ተመላልሶ ይሰጣቸዋል? እኔ ቃል እገባለሁ። አንድም ቀን ሳላጓድል ምግባቸውን ለማቅረብ፣ ተመላልሸም ለመጠየቅ ዝግጁ ነኝ። ለነገሩ የቃሊቲ ባለውለታዎቼም አይደሉ።

## የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ላይ ያወጣውን ሪፖርት በማጥቃት ወያኔ፣ (ከገፅ 1 የዞረ)

ይህንን የሰሞኑን የአገዛዙን የውሸት ዘመቻ በተመለከተ የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ ፓርቲ ሊቀመንበር እና የፓርላማ አባል ዶ/ር መረራ ጉዲና፥ አገዛዙ በዚህ ዘመቻው ማንን ሊያታልል እየሞከረ እንደሆነ እንደማይገባቸው መናገራቸው ተዘግቧል። ዶ/ር መረራ፥ ወያኔ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚስጥር እስር ቤቶች እና ማጎሪያዎች የለም ማለቱን በሚመለከት ሲናገሩ፣ ሌላው ቢቀር አምቦ አካባቢ ብቻ ሶስት የሚስጥር እስር ቤቶች እንዳሉ እንደሚያውቁ ገልጸዋል። አምቦ አካባቢ የሚገኘው የሃይለ ስላሴ ቤተ መንግስት፣ የሰንቀሌ ፖሊስ ማሰልጠኛ ማእከል እና ሆለታ የወታደሮች ካምፕ የሚስጥር እስር ቤቶች እንደሆኑ በቂ ማስረጃ እንዳላቸው ተናግረዋል። ዶ/ር መረራ ጨምረውም፥ ከምርጫ 97 በኋላ በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ዜጎች የታጎሩበት ዴዴሳ በኦፊሴል የታወቀ እስር ቤት እንዳልሆነ አስታውሰው፣ ለዚህ ሁሉ አስፈላጊው ማስረጃ እንዳለ ገልጸዋል።

የሚይዝ የሚጨብጠው የጠፋው ወያኔ ሰሞኑን እያካሄደ ባለው የስድብ እና የማስፈራሪያ ዘመቻ ከአሜሪካ መንግስት አልፎ ታዋቂ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችንና የእንግሊዝ መንግስትንም አካቷል።

## የኢትዮጵያው አገዛዝ በህጋዊ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ የሚፈጽመውን ግፍ ቀጥሏል... (ከገፅ 1 የዞረ)

ከሁለት ሳምንት በፊት አገዛዙ "መንግስቴን ሊገለብጡብኝ" ነበር በማለት የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን ማደን ሲጀምር ቤታቸው ከተከበበባቸው ሰዎች መሃል አቶ አብዩ አንዱ ነበሩ። ይሁንና በወቅቱ እሳቸው በስራ ምክንያት ቤታቸው ስላልነበሩ፣ የቤታቸውን መከበብ እንደሰሙ ካገር ለመውጣት መቻላቸውን በቃለ ምልልሱ ገልጸዋል።

አቶ አብዩ እንዲህ ባጋጣሚ ለማምለጥ እና ጉዳያቸውን ለማጋለጥ ባይችሉ ኖሮ፣ መንግስት በመገልበጥ ሙከራ ተከሰው ባሁኑ ሰዓት አርባ አንደኛው እስረኛ በሆኑ ነበር።

አገዛዙ ስልጣን ከተቆናጠጠበት ጊዜ ጀምሮ ይቀናቀኑኛል ብሎ የሚያስባቸውን ሰዎች በሙሉ በዘውግ ላይ በመመስረት የህገ-ወጥ ፓርቲዎች አባል ናችሁ ብሎ በመወንጀል እያሰረ እንደሚያንገላታ ይታወቃል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ቁጥራቸው የማይታወቅ ኢትዮጵያውያን ዜጎች በእስር እንደሚማቅቁ የሚታወቅ ሲሆን፣ አንዳንዶችም በእስር ቤት ከሚደርስባቸው እንግልት የተነሳ እንደሚሞቱ ከእስር ቤት በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚለቀቁ ሰዎች ይናገራሉ።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ** እና **በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org